# የኔ ሸበት

Welelaye2@yahoo.com

በቁርጥራጭ ሦስት መንግሥት
ስንገላታ ስንከራተት
ቱግ ብሎ በባዶ ቤት
ያስቀኛል የኔ ሸበት
ድሮ ፀጉሩ ነጥቶ እማውቀው
ቦርጭ ቢጤ ሆድ ነበረው
ድሮ የማውቀው ባለሸበት
ነበረ ቢያንስ የአምስት አባት
ይሆን ነበር ወይም ዶክተር
የድሮ ነጭ ባለፀጉር
መሪ ነበር ወይ የእድሩ
ያኔ እማወቀው ነጥቶ ፀጉሩ
እንደኔ እንዲህ የወረረው
ቢያንስ ሥልጣን ቤት ነበረው
ወይ ደጃዝማች ፊት አውራሪ
ወይ ዳሪክተር አስተማሪ
ይሆን ነበር የጦር መሪ
ወይ ቀኝ አዝማች ባላምባራስ
ይሆን ነበር ወይም አጃንስ
ቢጠፋ እንኳን ሌላው ቢቀር
የእቁብ ዳኛ ይሆን ነበር
ወይም ቅቤ ማር ነጋዴ
ብር ማግኛ ያለው ዘዴ
የታወቀ ባለ ሆቴል
ባለ ጋራዥ ባለ ኦፔል
ይሆን ነበር ባለ ወፍጮ
ብዙ ሰጪ ለመዋጮ
ብዩ ሳስብ የኔ ሸበት
መንጨፍረሩ በባዶ ቤት
ያስቀኛል እንደዘበት
ወይ ተምሬ ጫፍ አልደረስኩ
ወይ ዘምቼ አልተመለስኩ
በኔው ሸበት እኔው አፈርኩ
መሿለኪያ ወይ ካሳንችስ
ገዳም ሰፈር ሀብተጊዮርጊስ
ደጃች ውቤ ስልከሰከስ
እዛ ስጭር እዛ ሳምስ
ቀን በጠላ ባዶ ግሳት
ማታ በጠጅ ከንቱ ኩራት
በትንባሆ በጫት ሃዚም
ተተብትቤ ስስለመለም
በየቦታው ስርመጠመጥ
የሰው ወሬ ሳገላብጥ
በኑሮዩ ሳልለወጥ
እንደገና ጊዜው ከፍቶ
አመጽ ሸብር ተበራክቶ
የወንድሜ ማህል ጽናት
ተበርግዶ ጥይት ከፍቶት
የእህቴ የፊት ፀዳል
ተጨማልቆ በደም መግል
ያን አይቼ በፍርሃት
ካንዱ ዘመድ ወዳንዱ ቤት
እህል ሳልቀመስ በባዶ እግሬ
ከልደታ እስከ አቧሬ
ከቡራዩ እስከ ጊዮርጊስ
ከላም በረት እስከ ሳሪስ
ከመርካቶ  እስከ ጉለሌ
ከቃሊቲ እስከ ግንፍሌ
ከረምኩና ስንከራተት
ጨምሬበት ዳግም ስደት
እኔ ሆንኩኝ የዛ ውጤት
የታባቱ የኔ ሸበት
አዋረደኝ በባዶ ቤት
ለነገሩ በውጪ ሀገር
ጭራሽ የለም ጥቁር ፀጉር
መላጣውን ጌታ ወዶት
ገላገለው ከዚህ ሸበት
የሱ ደግሞ መጥፎ ችግር
ሲሸብት ነው ዳርና ዳር
ነፃ ወጥቷል ከዚህ ሴቱ
አለው ዘዴ በያይነቱ
አታርጉብኝ ብቻ ፍርጃ
ይወለዳል ነጭም ጥጃ
የማዝነው ግን የኔን ሸበት
ቢያደርግለኝ በሀገር ቤት
በማስታረቅ ባልና ሚስት
በበላሁኝ ስንት ሙክት
ሆኖ ቀረ እዚህ ከንቱ
የኔ ሸበት የታባቱ
እችል ነበር ልከልለው
እንዴት ከኔ ልሰውረው
እስከዛሬ ያልነጣችሁ
ካጉል ሸበት ያድናችሁ
ወይ ውለዱ ወይ ተማሩ
ነግዳችሁ ወይ ክበሩ
ላገራችሁ ወይም ሥሩ
ነጣጥታችሁ እንዳትቀሩ
ሸበት መጣ ደረሰብኝ
ምን ይሻላል እንዳትሉኝ
በቁርጥራጭ ሦስት መንግሥት
ስንገላታ ስንከራተት
ቱግ ብሎ በባዶ ቤት
ያስቀኛል የኔ ሸበት።

*ከወለላዬ ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ስዊድን/*
*July 3, 2008 Sweden*